# ኒዎሊበራሊዝም እና ጥገኛው ቡድን

(ክፍል ሁለት)

ዮናስ 09-24-14

‹‹ከራሴ ልምድና እኔ ከማከናውነው ተግባር በመነሳት የፕሬስ ነጻነት በኢትዮጵያ የለም ብዬ መናገር አልችልም፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት በተሰማራሁበት የሥራ መስክ ሙያውን እንደምፈልገውና እንደማውቀው ባለኝ አቅም መጠን ፕራክቲስ እያደረኩ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ የፕሬስ ነፃነት በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ የለም ብዬ ብከራከር የራሴን መኖር የመካድ ያህል ስለሚያስጠይቀኝ የለም ብዬ አልከራከርም፡፡›› በማለት የተናገረው የዛሬን አያድርገውና ቆዛሚዎቹ ለምርጫ 2007 በፕሬስ ነጻነት ስም ለቀለም አብዮት ተፍ ተፍ ሲሉ በነበረበት በዚያ ሰሞን፣ የገበያ አክራሪው አጫፋሪ ለሆነው ቪኦኤ የፎርቹን ጋዜጣ ማኔጂንግ ኤዲተር ታምራት ገብረ ጊዮርጊስ ነው፡፡

ታምራት ይህን ሲል የ‹‹እሰጣገባ››ው ፕሮግራም አዘጋጅ ፍፁም አልገረመውም፤ በእርግጥ እንዲገርመውም አይጠበቅም፤ ምክንያቱም ቀድሞ ነገር ታምራትን ለዚህ ውይይት ሲጋብዙት የሚሰጠውን መልስ በማወቃቸውና ተሳትፎውም ለጋዜጠኝነት ለሚዛናዊነት መርህ መገዛት በመሆኑ ነው፡፡

ታዲያ ለጋዜጠኝነት ሚዛናዊ መርህ ለመገዛት በመሻት ታምራት ለሰጠው አስተያየት ባለመደነቅ፣ አስቀድሞ ነገር ባሰቡበት መንገድና ሁኔታ ሰፊ ሰዓት ሰጥተው ሃሳቡን በጋዜጠኛነት ካባ፣ በቀለም አብዮት ንግድ ውስጥ የሚገኘው ተመስገን ደሳለኝን አጣጥለውታል፡፡ ተመስገን ደሳለኝ በሌለው መረጃ ‹‹የኢትዮጵያ መሬት ተቆርሶ ለሡዳን ተለግሷል›› ባለበት ዕሁፉ አብዮቱን ያደናቅፋሉ ብሎ ከጠረጠራቸው ሰላማዊ ተቃዋሚዎች መካከል ስለሰላማዊ ተቃውሞ ከተደበቁበት ምሽግ የወጡትን ‹‹ሌንጮ ለታ›› ‹‹አቦ ሌንጮ ለታ በባሌ ሲጠበቅ ገባ በቦሌ›› ሲል በተሳለቀበት መንገድ፤ ሌላኛው ሊበራሊስት ምሁር አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ሚዲያንና የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስታዊ ሥርዓትን በተመለከተ አዘጋጅቶት በነበረው መድረክ፤ ሊበራሊስት እንደሆነ የሚታወቀው ጋዜጠኛ ታምራት ስለሰጠው ምክንያታዊ አስተያየት በመቆጨት ‹‹አንተ ለሀብታም ስለምትጽፍ አይገባህም›› በማለት ወርፎት እንደነበር አይዘነጋም፡፡ ተመስገንም እንዲገባው

ባልፈለገው የፕሬስ ነፃነት ላይ በተጨባጭ የሌባና በምክንያት ያልተደገፈ ማብራሪያውን የገበያ አክራሪ ሃይሉን ለማርካት በማሰብ እንዲህ ብሎ እንደነበር አይዘነጋም፡፡

ከፍትህ ጀምሮ የነበሩት የህትመት ውጤቶች መዘጋት "መንግስት ምንም አይነት የሚዲያ ምህዳር በሀገሪቱ እንዳይኖር የሚፈልግበት ሁኔታ ነው" ብሎ "ከምርጫ 97 በኋላ ከህገመንስግቱ ድንጋጌ ውጪ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን በሚፃረር መልኩ ልዩ ልዩ አዋጆችና ድንጋጌዎች (የፀረሽብርተኝነት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የተመለከቱ አዋጆች) ወጥተዋል" በማለት ተናግሮ፤ "በመሆኑም እነዚህ ሁኔታዎች ኢትዮጵያ ውስጥ የፕሬስ ፍሪደም የለም ብለን እንድንከራከር በቂ ምክንያት ሆነዋል፡፡›› በማለት ለጣቢያው ገልጧል፡፡

አዋጆቹን በተመለከተ የወጡበትን ምክንያቶችና ህገመንግስታዊ መነሻዎቹን በመንግስት በኩል በተደጋጋሚ የተገለፀ ከመሆኑም በላይ ተገቢነታቸውን በተመለከተም በርካታ የመስኩ ምሁራን ባደረጉት ጥናት ማረጋገጣቸው ይታወሳል፡፡ ያም ሆኖ ግን ከህጎቹ መውጣት በፊት በጋዜጠኝነት ሽፋንና በምርጫ ታዛቢነት መታወቂያ መያዶቹ እና ፕሬሶቹ ተቀናጅተው በሀገሪቱ ሉዓላዊነት ላይ የቃጡት ሙከራ እና ስለአዋጆቹ አስፈላጊ መሆንና አለመሆን ማውራት ጊዜ መውሰድና ፋይዳ በሌለው ጉዳይ ላይ መጠመድ ስለሚሆን እንዝለለውና ወደጉዳያችን እናምራ፡፡

የመያዶችን፣ የተቃዋሚውን እና የፕሬሱን መጠላለፍና በፕሬስ ነፃነት፣ በህገመንግስታዊ መብቶችና በሰላማዊ ሰልፍ ሽፋን የተደረጉና በተደጋጋሚ በፍቺ የተጠናቀቁ ጋብቻዎችን በተመለከተ ከምርጫ 97 እና 2002 ትርክታችን ጋር አያይዘን በተመለከትነው አግባብ ሚስጥሩን ለመረዳታችን በቂ እንደሚሆን በመገንዘብ ሳይጸነስ ጨነገፈ እንጂ በቀዛሚዎቹ አሰባሳቢነትና በገበያ አክራሪው የገንዘብ ምንጭነት ተቋቁሞ ስለነበር አዲስ የጋዜጠኞች ማህበር ጀርባ ጥቂት እንፈታትሸና ሌላኛውን የእውነት ጫፍ እንያዝ፤ ይህን ጉዳይ ስንመለከት ‹‹የፕሬስ ነፃነት የለም›› ሲሉ የሚሟገቱ ወገኖች ከሚያነሷቸው የማተሚያ ቤቶች አሰራር በጋዜጠኞች ላይ እየተደረገ ነው ከሚሉቱ "እስርና አፈና" እንዲሁም ከመፃፍና የመናገር ህገመንግስታዊ ጥያቄዎች አንፃር ቢሆን ደግሞ የበለጠ ጉዳያችንን ያጠራልና በዚሁ አግባብ እንቀጥላለን፡፡

"በሀገራችን የፕሬስ ነፃነት ተረጋግጧል።" ከሚሉቱ ጋር የምስማማው ይህ ነፃነት በተግባርም የሚታይ ስለሆነ ነው፡፡ "የፕሬስ ነፃነት የለም" የሚል ስሞታ የሚያሰሙ ወገኖች

ራሳቸው ይህንን ስሞታቸውን በሀገሪቱ ውስጥ ታትመው በሚወጡ ህትመቶችና በሚሰራጩ የብሮድካስት አገልግሎቶች አማካኝነት ሲያስተጋቡ መስማቱ ራሱ የፕሬስ ነፃነት ለመኖሩ አንድ ማረጋገጫ ነው፡፡ የቅድመ ምርመራ ስጋትና ፍርሃት ሳይኖር በመንግስት ላይ ይርባም አይርባ ከማናቸውም አይነት የአስተሳሰብ/የአመለካከት ዘንግ ላይ ተነስተው ትችቶችን የሚያቀርቡ ህትመቶች ያለምንም ችግር ለስርጭት እየበቁ ስለመሆናቸው ሌላው ቀርቶ እነርሱ ቢክዱትም  የዛሬን አያድርገውና አብዮተኛዋን ፋክት ዳግም ወደኋላ ተመልሰን በማየት ብቻ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ከየትኛውም አገር በተለይ በአፍሪካ ካሉ የትኞቹም ቦታዎች እጅግ በተሻለ ሁኔታ ለመገናኛ ብዙሃን የሀሳብ ነፃነት መንሸራሸር ምቹና ታጋሽ የሆነ ድባብ የተፈጠረበት አገር ነው ያለን ብሎ መከራከር ከጤነኛ ዜጋ የሚጠበቅ እንጂ ካድሬ የሚያሰኝ አይደለም፡፡ ይሄ የፕሬስ ነጻነት በአሰራርና በተግባር ብቻ ሳይሆን ህገመንግስታዊ ጥበቃም ማግኘቱ በመሬት ላይ ያለ እውነት ነው፡፡ ቅድመ ምርመራ በአዋጅ መወገዱም እንዲሁ፡፡ መንግስት በማንኛውም አይነት የፕሬስ ስራ ውስጥ ጣልቃ እንዳይገባ ተከልክሏል በተግባርም እየታየ ነው፡፡ ጣልቃ የሚገባባቸው ሁኔታዎችም ካሉ በፍርድ ቤት ፈቃድ እጅግ በጣም ውስን የሆኑ ጉዳዮች ላይ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ ይህም ሆኖ መንግስት እነዚህን የገደብ አሰራሮች ሲጠቀምባቸው የማይታይበት ምክንያት ለፕሬስ ነጻነቱ ካለው ፍላጎትና ነጻነቱን ለመታደግ ካለው ቀናኢነት መሆኑን መቀበል ዴሞክራትነት ነው፡፡ እዚህ ጋር ታምራትን ማስታወሱም ቀናኢነት ነው። ስለዚህ ህጋዊና ህገመንግስታዊ ዋስትና አለ፤ ተቋማዊና የአሰራር ነጻነት አለ፤ ይሄ ነጻነት እንዲስፋፋና እንዲያብብ የሚፈልግ ጠንካራ የፖለቲካ ፍላጎት አለ፡፡ በአገራችን የፕሬስ ነጻነት የቅንጦት ጉዳይ ሳይሆን የዲሞክራሲያችን ዋስትና እና የህልውና ጉዳይ መሆኑም ሊዘነጋ አይገባም። በዚህ ረገድ  ለፕሬስ ነፃነት ተግባራዊነቱ የሚታገል መንግስት ባለበት ሀገር ውስጥ የፕሬስ ነጻነት አልተረጋገጠም፤ ወይም ነጻነቱ ተነፍጓል የሚለው አሉባልታ/ ቅሬታ በእኔ እምነት  መሰረቱ የቀለም አብዮትን ጉዳይ ማስፈጸምን ያለመ የነበረ ግን ደግሞ ባንቋሸሹት ህግ ጥጉን የያዙበት ሁኔታ መፈጠሩ ነው ቁም ነገሩ ፡፡

ስለሆነም  ሁለት የማይገናኙ ነገሮች ለማገናኘት ከመሞከር የሚነሳ ጉዳይ የማስፈጸም አጀንዳ ነው ብለን የነበረው ይኸው በተግባር እንደታየው የትም ስለማያደርስ ነው ፡፡ ከህትመት ውልም ጋር ተያይዞ  ብዙ ተብሎ የነበረ ቢሆንም ነገርዬው ለቀለም አብዮት ማመቻመችና ትንሽ ትልቁን ማራገብ ስለሆነ እንጂ  የህዝብ (የመንግስት) ማተሚያ ቤቶች ለሁሉም እኩል የሆነና ፍትሃዊነቱ የማያጠያይቅ ስታንዳርድ ውሎችን ከመቅረፃቸው ጋር

የተያያዘ ነው፡፡ እነዚህን ስታንዳርድ ውሎች እንደምንም ጎትተው በማምጣት ነው ቅድመ ምርመራ ነው በማለት የሚከራከሩት። ይህን የሚሉ ወገኖች የመጀመሪያ አነሳሳቸው ውሉን "አዋጅ ነው"፤ መንግስት አዲስ አዋጅ፣ አዲስ መመሪያ አወጣ ብለው ነው የሚነሱት፡፡ መጀመሪያ በመመሪያና በውል መካከል የሰማይና የምድር ያህል ልዩነት መኖሩን አጥተውት አልነበረም፡፡ በብርሃንና ሰላም እና በአስፈፃሚው መንግስት መካከልም እንዲሁ የሰማይና የምድር ያህል ልዩነት እንዳለ ያውቃሉ። ብርሃንና ሰላም ንብረትነቱ የመንግስት ይሁን እንጂ በንግድ ህግ መሰረት የሚንቀሳቀስ አትራፊ የንግድ ድርጅት ነው፡፡ ስራውን የሚያከናውነው በፍታብሔር ህግና በንግድ ህግ መሰረት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ብርሃንና ሰላም እንደአየር መንገድ፣ አንበሳ አውቶቢስ ድርጅት እና እንደ ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች አገልግሎቱን ለደንበኞቹ እየሰጠ ገንዘብ እየተቀበለ ለትርፍ የሚሰራ ድርጅት ነው፡፡ ይሄ ድርጅት ከደንበኞቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት የሚመራው በውል ነው፡፡ ውሉ የሚገዛው በፍትሃብሄርና በንግድ ህጉ አማካኝነት ነው፡፡ አየር መንገድ፣ ኢትዮ ቴሌኮም፣ ኢ.ኤ.ኃ.ኮ፣ አንበሳ አውቶቢስ እና መሰል የልማት ድርጅቶች የሚሰጡትን አገልግሎት በተመለከተ ስታንዳርድ ውል እንዳላቸው ሁሉ የመንግስት ማተሚያ ቤቶችም ከበርካታ ደንበኞች ጋር የሚዋዋሉና የሚገናኙ እንደመሆናቸው እስከአሁን ወጥነት ያለው ውል ያለመዋዋላቸው ለምን ቆዩ ቢያሰኝ እንጂ ጉዳዩን ከህገ መንግስታዊ ጉዳዮች ጋር አገናኝቶ መንግስት እራሱ ለህገ መንግስቱ አይገዛም ማለት እራስን ማሞኘት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ይሄ ውል የሚመራው በፍትሃብሄር በንግድ ህግ መሰረት ነው፡፡ ስለዚህ አንበሳ አውቶቢስ የጦር መሳሪያ አልጭንም ብሎ እምቢ ሊል ይችላል፡፡ ህዝብ ላመላልስበት ነው እንጂ የጦር መሳሪያ በህገወጥ መንገድ ለማዘዋወር ወይም ኮንትሮባንድ ለማዘዋወር የጭነት አገልግሎት አልሰጥም፣ ህገወጥ የሆነ ስራ አልሰራም የሚል ውል ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡ ይህ በህግ የተፈቀደለት ነው፡፡ ስለዚህ ማተሚያ ቤቶችም ህግን የሚተላለፍ ይዘት ያለው ነገር አትሜ እንዳወጣ አልገደድም የሚል ድንጋጌ በውላቸው ውስጥ ማስቀመጣቸው ተገቢ እና የሚያስመሰግናቸው ነው እንጂ ቅሬታና ኡኡታ የሚያስነሳ ነገር መሆን እንደሌለበትም ተናግረን የነበረ ሲሆን ተቃዋሚውና ፕሬሱ በአንድነት በፈጠሩት ቁዘማ ነገሩ ቢቃለጥም መጨረሻው እነርሱኑ ጠልፎ ሊጥላቸው ችሏል፡፡

በመሆኑም፣ ተግባሩ ቅድመ ምርመራ እንዳይደለ እና ከህገ-መንግስቱ ጋርም እንደማይጋጭ አፋችንን ሞልተን ብንመሰክር ያምርብናል ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ የብሪቲሽ የአሳታሚ ኢንዱስትሪዎች ማህበር ያወጣው ረቂቅ ድንጋጌ ውል የሚለው አሳታሚው ወይም አታሚዎች ህገ-ወጥ ይዘት ያለው ፅሁፍ አላትምም ማለት ይችላሉ ብቻ ሳይሆን የሚያበቃው "ስም የሚያጠፉ" ብሎ ይጨምርበታል፤ የስም ማጥፋት ይዘት ያለው ወይም ደግሞ የሌሎችን የንብረት መብት፣ የፈጠራ ችሎታ መብት እና የኮፒራይት ወዘተ የመሳሰሉት የአእምሮ ንብረት ጥበቃ መብቶች የሚጥስ ይዘት ያላቸው ከሆኑ፣ ከሌላ ሰው መጽሀፍ ላይ ተቀድቶ የተወሰደ ከሆነ አላወጣም ማለት ይችላል ይላል፡፡ ይሄ የሌላኛዋ የቀለም አብዮት አራጋቢ በሆነችው ሃገረ እንግሊዝ የማተሚያ ኢንዱስትሪ የሚሰራበት ነው፡፡ የቀለም አብዮቱ ወላጅ በሆነችው ሃገረ አሜሪካ የማተሚያ ድርጅት ማህበር ያወጣውን ጋይድ ላይንም ብንመለከት ማተሚያ ቤቶች ህገ-ወጥ ነገርን አላትምም ማለት ብቻ ሳይሆን ካላቸው የፖለቲካ አቋም ጋር የማይስማማ ይዘት ያለው ጽሁፍ ለህትመት ከቀረበላቸው አልፈልግም ብለው መጣል ይችላሉ፤ መብታቸውም ነው ይላል፡፡ ነገር ግን በዘር፣ በጎሳ፣ በሃይማኖት፣ ወዘተ ደንበኛ መምረጥ አይችሉም፡፡ በመሆኑም ይህ አለም አቀፍና የተለመደ አሰራር ነው፡፡ ስለሆነም በየቦታው መንግስትን ያለውሎው አፋኝ ነው ማለትና ቅድመ ምርመራ በተዘዋዋሪ መንገድ መጣ የሚል ሀሜታና ስሞታ ማቅረብ ተገቢ አይደለም ብለን የነበረውም ለዚሁ ነው፡፡

የስራ እድል ለማግኘት ለአሜሪካ ውጭ ጉዳይ የኢሚግሬሽን መ/ቤት የሚቀርቡ ልቦለድ ማመልከቻዎች ላይ መሰረት አድርጎ አገሪቷ ውስጥ አፈና አለ ሲሉ የነበሩት እነ ሰማያዊ እራሳቸው አፋኞች ስለመሆናቸው ይኸው ምክር ቤቱ በኡኡታ ድምጹን እያሰማ ነው ፡፡ ማንም ሰው ከአገር ውስጥ ተገዶ እንዲወጣ የተደረገበት አሰራር የለም ስንል ሲጮህ፣ ሲያጮህና ሲያጯጩህ የነበረው አንድነትም ይኸው በራሱ ቤት በተነሳው እሳት ቁም ስቅሉን እያየ የሚገኘው ትክክለኛውን አልሰማ ብሎ ነው፡፡

በሌላ ደረጃ የምርጫ 97ን የተቃውሞ ሠልፍ በማስታወስና የአንድ ሰሞን ፋሽን ከነበሩት ሠልፍ መሠል ግርግሮች ጋር በማተያየት የቀለም አብዮት አራማጆች ሚናና ጉምጉምታን መመርመር ስለሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንጨነቃለን፤ ተጨንቀንም ሣናበቃ መሆን ያለብንን ሁሉ እንሆናለን ለምንለው ዜጎች ሁሉ ጠቃሚና ለተቃዋሚ ፓርቲዎቹም ምናልባት የማሠላሠያ ጊዜ መስጠትና ቆም ብለው እንዲያስቡ ማስቻል እንደሆነ በማመን ያደረግነውን ጥረት የሚሰማ ጠፍቶ ይኸው በምርጫው ዋዜማ ላይ ቅጥ አምባሩ ለጠፋ ትርምስ ተዳርገው አርፈዋል፡፡ ኧረ ቀስ ስንላቸው ታብየው ለነበሩት እነሰማያዊ አብዛኞቹ የሃገር ውስጥ ጋዜጦች የተደረጉትን ሠልፎች ከምርጫ 97

ዋዜማ ላይ ከተደረገው የተቃውሞ ሠልፍ ቀጥሎ ከ8 ዓመታት በኋላ የተደረገና የዚህ ምክንያትም የጠቅላይ ሚኒስትር መለሥ ዜናዊ ሞት እንደሆነ በመጥቀስ አንቀለጳጵሰዋቸው የነበረ ቢሆንም ሠልፉን ያከናወንነውና ያደራጀነው እኛ ነን በሚል የሰማያዊ እና አንድነት ፓርቲዎች አባላትና የበላይ አመራሮችም  የታሪክ ሽሚያ ውስጥ ገብተው የተተጋተጉ ጊዜ ነበር መጨረሻቸው ከሰሞኑ የሆኑትን እንደሚሆኑ ተናግረን ነበር ::

ይህ ግን በመሠረቱ ሥህተትና አስተዛዛቢ እንደሆነ በወቅቱ ስንናገር የስህተታቸው መሰረት የሆኑ ዋቢዎችን ጠቅሰን ነበር፤ እነዚህም "ጋዜጠኞች" እና የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች በዋናነት ሚሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ህዝቡና የውጭው ሚዲያ ነው፡፡ በምርጫ 97 ዋዜማ ላይ ቅንጅት የተባለው ፓርቲ በጠራው ሠልፍ በመሥቀል አደባባይ የተገኘው ሥፍር ቁጥር የሌለው ህዝብ ደረጃውን ከሠልፍነት ከፍ አላደረገውም፤ ያደረገው ካልሆነ ከቅንጅት አንፃር 50ሺዎችና 10ሺዎች የተገኙበትን ያን ግርግር መሰል  ሰልፍ እነሠማያዊ ፓርቲ ሠልፍ ብለው መጥራታቸውና በዚህም የልብ ልብ ተሰምቷቸው የመታበያቸው ውጤት ነው ለዛሬው ትርምስ ያበቃቸው። በውጭው ሚዲያ እንደምንሠማውም ዴያስፖራው አካባቢ 10ም ሆኑ ሰማኒያ፤ 20ም ሆኑ 40 በየኤምባሲው ደጃፍ ላይ የሚያሠሙት የተቃውሞ ድምጽ (ብልግናቸውን ላለመጥቀስ ነው) በሠላማዊ ሠልፍ  ስም ተመዝግቦ የሚዲያ ሽፋን ሲሰጠው በማየት ዋናውን የፖለቲካ ስራ ትተው በአስር እና ሃያ ሰዎች ግርግር መቆዘማቸው ነው ለዚህ ያበቃቸው፡፡

ስለሆነም  የሠልፈኛው ቁጥር መብዛትና ማነስ የሠልፉን ስም የማይለውጥ ስለመሆኑና በሂደቱም እውቅናና ፈቃድ ከመጠየቅ ጀምሮ ያለው አቀራረብና አፈፃፀም ተመሣሣይ የነበረ መሆኑም ግልፅ ነው፡፡  የሆነ ሆኖ የመለሥን ዴሞክራሲያዊነት፣ የመለስን የመጠቀ ፖለቲከኝነት ጥላሸት ለመቀባትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ቀስ እያለ እየባሠ እና እየጎላ የመጣውን ስብእናቸውን ለማቆሸሽ ከስሜትና ቅናት በመነሣት የመለሥን ዘመን ሲያወግዙ የከረሙ ፓርቲዎችና አመራሮች ዛሬ እርስ በእርስ እየተወጋገዙ የመሆናቸው ምንጭ ዋናውን ስራ በመዘንጋት ትዝታ ላይ ተንጠልጥለው ለማለፍ በመሻታቸው ነው ። ይህ መሠረት የተጣለውና ፓርቲዎች ተንጫጩም ተሠለፉም አሁን ደግሞ ተፋተውም ምንም እንኳን ከእነርሱ ባይጠበቅምና ስነስርአት ባይሆንም መጠላለዝ የቻሉት በመለሥ ስለመሆኑና መለሥ ስለመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ታግሎ በማታገል፣ ሠርቶና አሰርቶ ባመጣው  ውጤት መሆኑን መደለዝና መፋቅ አይቻልም፡፡ ይሁን ቢባል እንኳ

መለስ በሥራው ያገኘው ሥም ነውና ከመቃብር በላይ ሁሌም ሲታወስና ሲዘከር የሚኖር መሆኑን መዘንጋት ተገቢ አይደለም፡፡

ንግባእኬ ሃበ ጥንተ ነገር እንዲሉ ዓበው ወደ ጥንት ነገራችን ስንመለሥ ከሰማያዊ ፓርቲ ጋር እንገናኛለን፡፡ ሰማያዊ ፓርቲ በሥም በሠማያዊነት ለፅድቅ የመጣና ሃይማኖታዊ ተቋም የሚመሥላቸው ብዙዎች ነበሩ፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ ፓርቲው እንደፖለቲካ ፓርቲ የፖለቲካ ፕግሮራሙን እና ፖሊሢውን ባለማስተዋወቁ አልያም የሌለው በመሆኑ፣ አልያም በኩረጃ የቀመረው በመሆኑ ከእፍረት ለመዳን ይመስለኛል፡፡ ስለሆነም  ምንም እጁ ላይ የለምና ስራውን በእግርና በምላሥ መጀመር ተገቢ ነው ብሎ በማግኘቱ እና ለዚህም የተመቹ ወቅታዊ አጀንዳዎች የነበሩ በመሆኑ ወደተቃውሞ ሠልፍ አመራና  ስራውን በሠልፍ መሰል ግርግር “ሀ” ብሎ ጀመረ፣ በወቅቱ በተገኘው ህዝብም ደስታው ወደር የለሽ እንደሆነ በጠላቱ ጠላት የተሠባሠቡ የፓርቲ አመራሮችና ጋዜጦች ጉዳዩን አደማመቁለት፡፡ ከዚያም የሠማያዊ ፓርቲ  አመራሮች የጋዜጣ ፊት ማዳመቂያ ሢሆኑም እራሣቸውን ቆለሉና በሁሉም ላይ አለን ሲሉ ጮክ አድርገው መዘመር ጀመሩ፡፡ አንድም አንኳ የምርጫ ዙር ተሣትፎ ኖሮት የማያውቀውና ገና ወፌ ቆመች ደረጃ ላይ ያልደረሠው ሠማያዊ ፓርቲ ዛሬ ሃገሪቱ ላይ ሠፊ ልምድ ካካበቱትና በተቃውሞ ፖለቲካ ተፈትነናል ከሚሉት በርግጥም ከተፈተኑቱ በላይ ማን እንደኔ ሲል በየተጠራበት  መደንፋትንም “ለ” ብሎ ቀጠለ። ዳሩ ግን  በሠላማዊ ሠልፍ የሥልጣን እርካብ ላይ የወጣ ፓርቲ የለምና አልሆነለትም፡፡  የእነግብጽ አይነቱ መስሏቸው ከሆነ የግብጽ ጉዳይ በመሠረቱ የተለየና ጉዳዩም ሠልፍ ሣይሆን በተደራጁና ሠፊ ልምድ ባላቸው ፓርቲዎች የተመራ መሆኑንም ብንናገር አልሰማ አለና ግርግሩን  ገፋበት፡፡  በኛ ሃገር ተጨባጭ ሁኔታ የግብጽ አብዮት የሚመጣበት መሠረታዊ ምክንያት ባይኖርም ከግብጽ አብዮት በሥተጀርባ ያለውን ጠንካራና የገዘፈ ፖለቲካ እና ፖለቲከኝነት ያልተገነዘቡት እነ ሠማያዊ ፓርቲ ያን አብዮት ላያገኙት  በመመኘታቸውም  ሊያፍሩ  እንደሚገባና ተመልሶ እንደሚልጣቸው ስንነግራቸውም አልሰማ አሉና ግርግራቸውን ተያያዙት፡፡

በተመሣሣይ አንድነት የተባለው ፓርቲ ለይስሙላ የሠማያዊ ፓርቲን ሠልፍ በአፉ ቢያደንቅም በተበለጥኩ ትምክህት ከመሬት ተነስቶ በደመነፍስ ያደረገው ሠልፍ ለተመሣሣይ የሃይማኖታዊ ተቃውሞ ሠለባነት መዳረጉን በአይናችን አይተን ይቅርባችሁ ብንልም የሚሰማን አልነበረም፡፡ አንድነት ደግሞ ያች ያገኛትን ምልክት ተጠቅሞ ሠማያዊ ፓርቲ  በሰልፍ መሰል ግርግሮች መጠመዱን እንደ ሽንፈት ወይም እንደ

ፖለቲካ ስራ ቆጥሮ በተከታታይ ሰልፍ ለማድረግ መዘጋጀቱን፤ ሰማያዊ ፓርቲም እሾህን በሾህ ነው እንዲሉ ለአፉ አንድነትን አድንቆ በተግባር ግን የሠልፍ ሽሚያ ውስጥ መግባቱ ጉዳዩ በርግጥም የእኔ እበልጥ ፍትጊያ እንጂ ህዝብን መሠረት ላደረገ ዴሞክራሲያዊ ለውጥ አለመሆኑን ተናግረን በነበረው መሰረት ፓርቲ ከፓርቲ ጋር የነበረው ፍትጊያ ወደግለሰብ ደረጃም ወረደና ይኸው እንዳልናቸው እየለመጠጣቸው ነው፡፡

በሠላማዊ ሠልፍ የሚቀየር ታሪክ ባይኖርም ግን ሠላማዊ ሠልፍ የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አንዱ መግለጫና ጠቃሚ የትግል ሥልት መሆኑን ግን መካድ አይቻልም፡፡ ሆኖም ግን እንዲህ ዓይነት ሠልፎችም ቢሆኑ የሚዘጋጁት የፓርቲዎችን ፕሮግራሞችና ፖሊሲዎች መሠረት አድርገው በበሠለና በሰለጠነ መንገድ ግባቸውን እንዲመቱ ሆነው ነበር፡፡ ዳሩ ግን ሰማያዊ ፓርቲና አንድነት  የአንድ ሰሞን አጀንዳ ከሆነው ጋር ሁሉ በመንጠልጠል አባዜያቸው አክራሪ ከሆነው ሙስሊም ህብረተሠብ አተርፋለሁ ብለው ምናልባት ካላቸው ከፕሮግራማቸው ወይ ከፖሊሲያቸው ያልተቀዳ መፈክር ሲያሠሙ መዳከራቸውም ዛሬ ከገቡበት ማጥ ሊያወጣቸው ይቅርና ለገቡበት ማጥም በራሱ አንድ ምክንያት ሊሆን ችሏል።

የሠማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት ሰልፍ ባደረጉ ማግስት በያለበት ይነከሩ ነበርና በፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ሞጋች ፕሮግም ላይ ሊሞግቱ በዚያ ሰሞን ቀርበው ነበር፡፡ ከሞጋቻቸው የቀረበላቸው የመጀመደሪያ ጥያቄ “ፓርቲያችሁ የሚወክለው የትኛውን ማህበረሠብ ነው?” የሚል ነበር እሣቸውም ሲመልሱ አንቱ የተሠኙበትንና ከአብዮቱ በፊት የነበረ ልደት ቀናቸውን በመዘንጋት፤ አልያም አንቱ ተሠኝተው አንቱ ያሰኟቸውን ከአብዮቱ ዘመን በፊት የነበሩ ወላጆቻቸውን ትተው ከ66ቱ አብዮት በፊት የነበረው ዜጋን ፓርቲያቸው እንደማይወክልና የአዲሡ ትውልድ ፓርቲ ለአዲሡ ትውልድ መሆኑን ተረኩ፡፡ በርግጥ ይህን ጥያቄ በዚህ መልክ ከመለሡ በኋላ በሞጋቻቸው ለቀረበላቸው ተከታታይና የሚሞግቱ ጥያቄዎች ሊቀመንበሩ ሲመልሱ ቆመንለታል የሚሉትን አዲስ ትውልድ ትተው አልያም ወጣቱን ነጥለው ሣይሆን፤ ስለህዝብ ማውራታቸው ፓርቲያቸው ግራ የተጋባ እና ፕሮግራም አልባ ስለመሆኑና መሪዎቹም ግራ የተጋቡ የሥልጣን ጥመኞች መሆናቸውን ያረጋገጠልን ጥሩ አጋጣሚ ነበር፡፡ ይህንኑ የሙግት መድረክ ተከትሎም በተለያዩ ጋዜጦች ላይ የፓርቲያቸው አባሎች ሊቀመንበሩ ላይ የነቀፌታ መአቱን ማውረዳቸው የፓርቲውን መርህ የለሽ አቋም የሚያረጋግጥ ሲሆን

የፈሩት ይደርሳል ሆነና ይኸው የምክር ቤት አባሎቻቸውን ጭምር ወግዱ በማለት ጸረ ዴሞክራሲያዊነታቸውን በይፋ እያረጋገጡ ነው፡፡

በአጠቃላይ በሠማያዊ ፓርቲም ሆነ በአንድነት በኩል የተደረጉት  የአንድ ሰሞን ሰልፍ መሰል ግርግሮችና የሚሊዮኖች ድምጽ ጂኒ ቁልቋል ለራሳቸውም ድምጽ ሳይበጅ እየናጣቸው ነው። በምርጫ 97 ዋዜማ ላይ መስቀል አደባባይ ላይ የፈሠሠውን ወጣት የተመለከቱት የቀለም አብዮት አራማጆች ምርጫው እንደ ዩክሬን ጆርጂያው ብርቱካናማ አብዮት ይቀየር ዘንድ በታዛቢ ቡድን እና በግብረ ሠናይ ድርጅት ሥም በላኳቸው ቅጥረኛ ኃይሎች በኩል ሞክረው የነበረ መሆኑ አይዘነጋም። ከቅንጅቱ አመራር አካላት ጋር መክረውና ዘክረው ሲያበቁ ሥራቸውን ምርጫው ገና ሣይካሄድ ቅንጅቱ የአሸንፈናል አዋጅ እንዲያሥነግር በማድረግም ጀምረው የነበረ መሆኑ ይታወሳል። ብልሁ መንግስትና ገዢ ፓርቲ በነበረው በሳልና ጥበብ የተሞላ ፖለቲካዊ ልምድ የህዝቡ ጨዋነት ታክሎበት ባይቀዘቅዝ ኖሮ ይደርስ የነበረውን ጥፋት መገመትም አይከብድም፡፡ ይህ የከሸፈባቸውና ግርግር ባዩበት የማይጠፉት የቀለም አብዮት አራማጆች በለጋሽ ሃገራት ሥም  በሃገር ውስጥ ገብተው ሠማያዊ ፓርቲን ሊጠልፉ እያመቻቹት መሆኑን እራሣቸው የፓርቲው ሊቀመንበር ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት መናገራቸውን ማድመጣችንና ማንበባችንም የቅርብ ጊዜ ሁነት ነው፡፡ ታሪክ እራሡን ይደግማል እንዲሉ ኢንጂነሩ ከ35 ሃገራት የተወከሉቱ ስብስቦች ባዘጋጁት መድረክ ላይ ተገኝተው ስለ ኢትዮጵያ መፃኢ ሁኔታ መዶለታቸውን እና “የግብጹ አብዮት የሚደገም ይመስልሃል?” የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ተገቢውን ምላሽ ስለመስጠታቸው አውስተው በተመሣሣይ ከቅንጅቱ በከፋ ሁኔታ የ2007ቱን ምርጫ ከወዲሁ ስለማሸነፋቸውም ማወጃቸው እንዲሁ ይታወሳል፡፡ ይህቺን የተመኙት ታዲያ የመረጣቸው ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ አረፍ ሲላቸው እምቢኝ ቢሉ ምን ይገርማል።? ኢንጂነር ግዛቸውስ እምቢኝ ብለው ቢፋለጡ ምን ይደንቃል።? ይልቁንስ ከመደነቅና ሲሻችሁም ኢህአዴግ ላይ በማላከክ ስራ ከምትፈቱ የሚያዋጣችሁ ፖለቲካውን መስራት እንደሆነ አሁንም በድጋሚ ልንመክራችሁና ልንዘክራችሁ እንወዳለን፤ ምክንያቱም እኛም ሆንን ባጠቃላይ አገሪቱ ጠንካራ የተቃዋሚ ፓርቲ ያስፈልገናልና ነው።